# <u>የሰሞኑ የግንቦት ሽርጉድ ፣</u>
# <u>ለወያኔ ተባብሮ ለማደሩ፣ በሕዝብ ቋንቋ ይናገሩ!</u>

**ከዳንኤል ዘበርጋ**

ወያኔ ቢነግስ በግንቦት፣ ኤርትራን ቢገነጥሉብን በግንቦት፣ ወያኔ የህዝብ ድምፅ ቢነጥቅ በግንቦት፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ቢበተን በግንቦት፣ ታላቁን የሕዝብ ልጅ ፕሮፌሰር አሥራትን ብናጣ በግንቦት፣ መንግስቱን ለመጣል የተደረገዉ መፈንቅለ መንግሥት ቢጨናገፍ በግንቦት፣ የኢህአፓ አንጃዎች በከርቸሌ ክፉ አደጋ ቢያደርሱ በግንቦት (የከርቸሌ ግንቦቴዎች አሁንም አገርሽቶባቸዉ ዉር ዉር እያሉ ነዉ።) የዉጭዉን የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አንድነት ብርሃኑና አንዳርጋቸዉ መከፋፈል የጀመሩት በግንቦት፣ አሁን ደግሞ ታላቁ ሴራ በግልገል ፋሽሽቶች ቢጠነሰስብን በግንቦት። የማያልቀዉ የግንቦት ጉድ ሰሞኑን ምን ሊያሳየን ይሆን?

ከፋሺዝም ባህሪያት ዋናቹ ሕዝብ የሚለዉን እያወሩና እየዋሹ ስለእናት አገርና ስለ ዴሞክራሲ እየሰበኩ የተጨቆነ ህዝብን ጥያቄ እያስተጋቡ የህዝብን ትግል ትቢያ ማልበስና ለስልጣን ሲበቁም ጭቆናና በደልን በባሰ ሁኔታ መቀጠል ነዉ። ይህ ደግሞ በአገራችን በደርግም ሆነ በወያኔ ሻእቢያ ያየነዉ ሲሆን ይባስ ብሎ ደግሞ ተቀዋሚ ነን በሚሉ ድርጅቶችና ግለሰቦች በሰፊዉ ተግባራዊ እየሆነ ነዉ።

ባለፈዉ ሁለት -ሶስት ዓመታት እንኳን የህዝቡን ስሜት እያዳመጡ፣ ጥያቄዉንም እያነሱ በማከያዉ ትግሉን እያሽመሽመዱ የህዝቡን ስሜት በክፉኛ ሁኔታ ሲጎዱት ተመልክተናል። እንዳየነዉም ሕዝብ ቅንጅትን ሆ ብሎ ሲመርጥ የደነገጡ- እንደነሱ አባባልም መሰበር ያለበት የትምክህተኛነት ጎራ ብለዉ ከራሱ በቅንጅት ዉስጥ ከነበሩና ከዚያም ዉጭ የተሰባሰቡ ሓይሎች የሕዝብ የሆነዉን አንድነት ሳይሆን የዉጭ ሃይሎችና ዘራቸዉ ከየድርጅቱ ያሰባሰባቸዉ ወገኖች የሚሟገቱለትን ጎሳ ጠቀስ ሥርዓት በሰተመጨረሻዉ ከወያኔ ጋር ተባብሮ ያለጠንካራ ተቃዉሞ ለማንሰራፋት እያሴሩ ነዉ። <u>*እስካሁንስ ምን አደረጉ? ምንስ ሊያደርጉ ነዉ?*</u>

1. በመጀመሪያ ዉጭ ባሉ የቅንጀትና የሕብረት ደጋፊዎች ይደረግ የነበረዉን የጋራ ትንቅንቅ አኮላሹ (ለዚህም አንዳርጋቸዉ አሁን ከእርሱ የተለዩ ሰዎችን በማሳሳት ጭምር ከሕብረት ጋር ያለዉ ግንኙነት በለንደን ላድብሮቭግሩቭ በሚባል ቦታ በግል ኮንና እንዲበላሽ ሲያደርግ ብርሃኑ መዋ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በአሜሪካ የተቃዉሞ ሰልፍ መደረጊያ ቀን ግንቦት 15 ይሁን 16 በሚል ሰንካላ ምክንያትና በግልጽም ሕብረትን ለቅንጅት መሪዎች መታሰር ተጠያቂ ናቸዉ በማለት በቅንጅትና ህብረት ደጋፊዎች ዉስጥ ክፍትተ እንዲኖር ያደረገዉ ዘመቻ የሚጠቀሱ ናቸዉ)

2. የአለምአቀፍ ቅንጅት አመራር ብለዉ ራሳቸዉን በመሰየም በቅንጅት ደጋፊዎች መሃከል መለያየት እንዲፈጠር አድርገዋል።

3. ሕብረት ያስተላለፈዉን የቀዉጢ ጊዜ ግብረ-ሓይል ጥሪ ተግባራዊ እንዳይሆን ለማድረግና በተለይም የቅንጅት ልባዊ ደጋፊዎችን የሚያሸሽዉን ትብበር ለነፃነት (AFD) የሚባለዉን ለማቋቋም ስምምነት በመፈረም በዉጭ ያለዉን የአንድነት ደጋፊ ሃይል እንዲከፋፈል ከማድረግ አልፈዉ አላሰፈላጊ ቃላት

በግለሰቦች እንዲወረወሩና የደከሙና ተስፋ ቆርጠዉ የነበሩ የፀረ- አንድነት ሓይሎች እንዲያሰራሩ የሚያስችል ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡ ተለጣፊ ድርጅቶችን ለማቋቋምና ኅብረትን ለማፍረስም ሞክረዋል -የጋምቤላ ድርጅት ሲፈጥር የሞከረዉ የአሁኑ ግንቦት 15-18 ቲያትር ቀንደኛ ተዋናይ ራሱ ምስክር ነዉ፡፡

4. በኢትዮጵያዊነት ላይ በፍፁም የማይደራደሩትንና በፀረ-ወያኔ አቋማቸዉ ላይ ለአፍታም እንኳን የማይታሙትን ግለሰቦችና ድርጅቶች በሰፊዉ አዉግዘዋል (ከድርጅት እነኢሕአፓንና ከግለሰብ እነዶክተር ታዬን መጥቀስ ይቻላል)፡፡ በተቃራኒዉ ደግሞ በአገርና በዘርም በመቅረብና በማሰባሰብ የወያኔ ጋኔናዊ የዘር ልክፍት በዉጭዉ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ዉስጥ እንዲስፋፋ ሌት ከቀን ሰረተዋል አሁንም እየሰሩ ነዉ፡፡

5. ኢትዮጵያን የሚመለከት የሰብአዊ መብት ህግ (HR2003) በአሜሪካን መንግሥት እንዲፀድቅ የተወሰኑ ሀቀኛ ሃይሎች የጀመሩትን ዘመቻ እነርሱ ዋነኛ በመምስል ከወሰዱ በኋላ በግማሽ ቀርቶ ከቁም ነገር እንዳይዉልና የሕዝቡም ስሜት እንዲነካና ተስፋ እንዲቆርጥ አድርገዋል፡፡ ከዋነኛ ተዋንያኖቹም መሀከል ከፊሎቹ ተለጣፊ የሴት ማህበር ለማቋቋም ሲጥሩ ከፊሎቹ ከመድረክ ሸሽተዉ ከሰነበቱ በኋላ አሁን ለዚህ ሴራቸዉ ብቅ ብቅ አያሉ ነዉ፡፡

6. በየድረገፁ በአገርቤት ያለዉ ተማሪ ካለስልት እንዲንቀሳቀስ ጥሪ በማድረግ በፀጥታ ሃይሎች እንዲመታና ተስፋ መቁረጥ እንዲነግስ አድርገዋል፡፡

7. እንደኤፍሬም ይስሃቅ አይነቱን በመቅረብ የህዝቡን ሞራል በሚነካ መንገድ የቅንጅት መሪዎች ይቅርታ ጠይቀዉ እንዲፈቱ አድርገዋል (የዚህም አላማ አክራሪ የሚሏቸዉ እንደነ ሓይሉ ሻዉል ያሉት አሻፈረኝ ብለዉ እሥር ቤት እንዲቀሩ -የነ ሙሉነህ አልፈርምም ብሎ ማላዘን የዚሁ ጠለፋ ሴራ ክፍል ነበር- ይህ ባይቻል ደግሞ በፀረ-ወያኔ ትንቅንቅ የተጎዳዉን ሕዝብ ቅስም ለመስበርና ህዝቡ ለቅንጅት ያለዉ ስሜት እንዲቀዘቅዝ የተሸረበ ሴራ ነበር)፡፡

8. የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱ በኋላ ደግሞ የቀረዉ አባልና ደጋፊ ጎራ ለይቶ አሳፋሪና ተራ በሆነ ስድብና ዘለፋ እንዲታመስ ሲያደርጉ፣ ለወትሮዉ የጠነከረ አንድነትና የቆየ ተሞክሮ ያለዉ ወያኔም በእጅጉ የሚፈራዉ የሚባለዉን ኢህአፓ በአጉል ሰዓት የድርጅቱን ሳይሆን የህዝቡን ሞራል ለመስበር ቅንጅት ዉስጥ ከነበሩና ትገሉን እየጎዱ ካሉ የወንዝ ልጆቻቸዉ ጋር ዉስጥ ለዉሰጥ በማሴር ጨዋነት በሌለዉና የህዝቡን ሞራል ለመጨረሻ ጊዜ ለመስበር በማሰብ በአሳቻ ጊዜ ከድርጅቱ በመገንጠል የተቀዋሚዉ ጎራ በአለም አቀፉ ሕብረተሰብ መሀከል ሳይቀር በአሉታዊ ገፅታ እንዲታይ አድርገዋል፡፡

9. ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደነሓይሉ ሻዉል ያሉትን ግለሰቦች የኢትዮጵያ ጠላቶች በማለት እንደሻእቢያዉ ኢሳይያስና እንደአነጉ ዳዉድ ያሉትን የኢትዮጵያ ወዶጆች በማደርግ አቅርበዋል፡፡

10. ዉጭ ያሉ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ስብስብ አባላት የራዲዮ ስርጭት ለመጀመር የሚያስችል የርዳታ ዘመቻ ዕቅድ በመስረቅና ለአዉሮፓ ህብረት በማስገባት እንዲሰናከል ሞክረዋል።

11. ጭራሽ በዉጭ ነዋሪ በሆነዉ የኢትዮጵያ ህበረተስብ ላይ ስድብና ዘለፋ አካሂደዋል፤(በቅርቡ አንዷ የደቻሳ ምርኮኛ ብላ በእንግሊዝ ያለዉን የኢትዮጵያ ህብረተሰብ በኢትዮጵያን ሪቪዉ ድረገፅ ስትዘልፍ በተመሳሳይ ደግሞ ክንፉ ኢትዮጵያ ዛሬ በተባለዉ ድረገፁ አበሻዉን አብጠልጥሏል።)

12. ትግሉን የባሰ ለመጉዳት ምናልባትም በአንድ ወገን የመሣሪያና የሕቡዕ ትግል የሚያካሂዱ አካላትን ስርጎ ለመግባትና በሌላዉ በኩል ደግሞ ወያኔ ታጣቂ እየቀለባችሁ ነዉ በማለት ህዝቡን እንዲያንገላታ ለማድረግና ገንዘብ ለመሰብሰብ ጦርነት አዉጀናል ይሉናል። የሚያስቀዉ ደግሞ እንደልባቸዉ የመንንገር ሰነድ የሚሰጧቸዉና ገንዘብ የሚለግሷቸዉ የወያኔ አጋር ሃያላን መንግስታት መባላቸዉ ነዉ -እስቲ ጉድ በሉ እነአሜሪካ ወያኔን እንዲወጉ ሲረዱኣቸዉ -ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት እንዲሉ።

የሚገርመዉ ደግሞ ይህንንና ሌላም ብዙ ያደረጉ ሓይሎች በየቦታዉ በመዶለት በመልኩ ለየት ያለ ሴራችዉን ከግንቦት 15-18 ባለዉ ጊዜ ሊያዉጁልን ነዉ። ***በነዚህ ቀናት ምን ሊከሰት ይችላል?***

1. እንደነአንዳርጋቸዉና ስዬ አብረሃ (ከአሁኑ በአባይ ሚዲያ ድረገፃቸዉ ጀምረዉታል) ያሉት የኢትዮጵያ ጠላቶችና ፀረ አማሮቹ ሲያሳድዷቸዉና ሲያንገላቷቸዉ የነበሩትን የእነ ፕሮፌሰር አሥራትን መስዋትነት ለመነገጃ በመጥቀስ ያፌዙበታል -ባለፉት ጥቂት ወራት እንኳን ደጋፊዎቻቸዉና አባላቶቻዉ (በየፓልቶክ ከፍሎችና ከአዲስ አባባ -እነ በፈቃዱ ደግፌና የነተመስገን ቡድንን ጨምሮ መአኢድ/መአሕድ እያሉ እንዳልኮነኑት ሁሉ)።

2. የግንቦቱን ምርጫ የህዝብ ድምፅ ይከበርን አላማ በማድበስበስ በአጋዚ ጦር የወደቁትን ህዝብ ልጆች እናስታዉስ በሚል ይቀልዱብናል ብዬ እገምታለሁ።

3. የህዝቡን ትገል ያኩላሹት ተንኮለኞች አዲስ ድርጅት ፈጠርን ብለዉ ዳቦ ይቆርሱና ከግንቦት በተያያዘ ስያሜ አዲስ ልብስ ለብሰዉ ይወጣሉ፣

4. የተለያዩ ግለሰቦችን ወደመድረክ ያመጡልንና ወደፊት ትግሉን እንደሚመሩልን በተዘዋዋሪ ሊያስገነዝቡን ይሞክሩ ይሆናል፣

5. ከህብረትም አባላት አንዳንዶቹ የዚሁ ሴራ ተባበሪ በመሆን በተዘዋዋሪ ህብረት እንደሚፈርስ ሊያበስሩልን ይችላሉ ብዬ በግሌ እጠብቃለሁ፣

6. ሴራዉን ተረድተዉ የሚያፈገፍጉ ንቁ ድርጅቶችን አንድነት አይፈልጉም በማለት ሊያሳጡ ይሞክራሉ፣

7. ሰንብተዉም ሰፊ ህብረት ብለዉ ግንባር ይፈጥሩልናል፣

8. አመፅም ጦርነትም እየተባለ ይፎከርና ምናልባትም ከሻእቢያ ተጠግተዉ በስተመጨረሻ እንደኢሕአፓዴ ነኝ የሚለዉ አንጃና የኦሮሞ ነፃ አዉጭ ድርጅቶች በድርደር ስም አገር ቤት ገብተዉ እንዲታገሉ ተፈቀደላቸዉ ይባልና ሁሉም በህብረት ዉስጥ ካሉት ወደጆቻዉ ጋር በመሆን ታማኝ ተቀዋሚ ይሆናሉ፤ ከሻእቢያም ጋር ያለዉ ዝምድና እንደቀድሞዉ ሆኖ ጨዋታዉ ይቀጥላል። በዚህም አምባሳደር ዶናልድ ያማማቶ የቀረዉ ተልዕኮ ተፈፃሚ ይሆንልታል (ታስተዉሱ እንደሆን ለሹመት ሲታጭ -አላሞዎቹ የቅንጅት መሪዎችን ማስፈታት፣በዉጭ ያሉ ተቀዋሚዎችን ጨምሮ ከወያኔ ማግባባትና የኤርትራና የኢትዮጵያን ወዳጅነት እንደድሮዉ መመለስ ነበር - ይህ ደግሞ የነፃነትና ትብበር አላማ ሲሆን -የአሁንም የእንአንዳርጋቸዉ ሰፊ ህብረት አላማ የዚሁ ማስፈፀሚያ ነዉ)።

## *ምን መደረግ ይገባዋል?*

1. የድርጅት አባላትና ደጋፊዎች ተንኮሉን ቀድሞዉ በመረዳት ህዝባዊ የሆኑ ፀረ-ወያኔ ግለሰቦችና ድርጅቶች የሴራዉ ተባበሪ እንዳይሆኑ ጫና ማሳደር፤

2. ለጊዜዉ ሊፈጠር የሚችለዉን ብዥታ እንደግለሰብ መመከት፤

3. ሀቀኛ ድርጅቶች በዉስጣቸዉ ያሉትን ሰርገ ገቦች በዚህ አጋጣሚ መመንጠርና ድርጅቶቻቸዉን ማጥራት፤

4. ፀረ-ወያኔዉን ትገል ማጠንከር፣ በአንድነት ሃይሉ መካከል ክፍተት ለመፍጠር የሚደረገዉን ሴራ ማክሸፍ፣ ችግሮችና ልዩነቶችን በተገቢዉና በጨዋ መንገድ መፍታት፤

5. ጊዜንና ጉልበትን በሙሉ በዉሉና በተገቢዉ መንገድ ለፀረ-ወያኔ ትግል ብቻ ማዋል፤

6. ሁኔታዎች ሊያመጡ ለሚችሉት ሁለገብ አሉታዊ ተፅዕኖ አስቀድሞ መዘጋጀት፣ በልበ ደንዳናነት መመከትና በጽናት መቆም፤

7. የታክቲክና ባህርይ ቅየራ በማድረግ ወዳጅ ከነበሩና ከካዱ ወገኖች ግመታ ዉጭ መሆን፤

8. እኩዮቹ በተለይ በአገር ቤት ሊያመጡ የሚችሉት ነገር ሰለሌለ ታጋይ ድርጅቶች የአገር ቤቱን ትግል በሁሉም መስክ በግንባር ቀደምትነት በጥንቃቄ መምራት፤

9. በድርጅት ያልታቀፍን ደግሞ የእነዚህ ሴራ ቶሎ በገሃድ እንዲወጣ በተገኘዉ መድረክ ማጋለጥ፤ በኢትዮጵያ ህልዉናና በህዝቡ የዴሞክራሲ ትግል ላይ የማይደራደሩ ድርጅቶችን በገንዘብ ማጠናከር፤

10. ድርጅቶች ራሳቸዉን እያፀዱና እያጠነከሩ፣ መጥፎ የትግል ታሪክ ካላቸዉ እየራቁ፣ በረጋ፣ በስከነና በስልት መተጋገዝና መተባበር።

በማጠቃልያም የሰሞኑ ትያትር

- እስከዛሬ በነበሩ ትግሎች ሁሉ በፈሪነትና በብተና የታወቁ፣
- የታጠቀ ሃይልንና ታጋይን የበተኑ፣
- በነበሩባቸዉ ድርጅቶች ዉስጥ ሰፊ መከፋፈል በመፍጠር አንጃ በአንጃ የሆኑና በድርጅቶች ላይ ድርጅቶች የፈጠሩ፣
- የህዝቡን የቤት መዋል አመፅ ያሰቀሙ፣
- ቂምና ጥላቻ በአማራና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያላቸዉ፣
- ከኢትዮጵያ ህዝብ ይልቅ ለዉጭ ሃይሎች ከበሬታ ያላቸዉ፣
- 3-4 አባላትን ይዘዉ በሌሎች ትካሻ ላይ ስብሰባዎችን ለመምራትና መግለጫ ለመስጠት ያሰፈሰፉ፤
- የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፈዉ የማይስጡ፣ የዘር ክፍፍልን አጥብቀዉ የሚቃዎሙና አክራሪ የሚባሉ ሃይሎችን አግልለናል ብለዉ ለወያኔ አቤቱታ ከማቅረብ የዘለለ ፋይዳ የማይሰሩ ያዉ ቢወቅጡት ተልባ የሆኑ ሃይላት፣

የአንድ ሰሞን ሽር ጉድ እንቅስቃሴ መሆኑን በመረዳት ወያኔዉን እንደሥርዓት የማስወገዱን ትግል ማጠናከር ይገባል።

**ኢትዮጵያ በነፃነቷ ዳር ድንበሯ ተከብሮ ለዘላለም ትኑር!**
**የህዝብ ድምፅ ይከበር!**
**የታሰሩ የፖለቲካ እሥረኞች ይፈቱ!**
**የዉጭ ቅጥረኞችና የዘረኞች ሴራ ይከሽፋል!**
**የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ የሚወጣዉ ከዉጭ ሀይል ተጽዕኖ ነፃ በሆኑ፣ ከወያኔ ባልተነካኩና ዘረኛ ባልሆኑ ሓይሎች የህብረት ትግል ብቻ ነዉ!!!**